# ቅንጅት

## <u>ደበበ - “ደደበ”</u>

( ከዮናታን )

በቅርቡ ወደ አሜካ የተጓዘው የቅንጅት የልዑካን ቡድን ተብዬ - አምስቱ የአመራር አባላትና አጃቢ.ዎቻቸው፣ በአንድ ስብሰባ ላይ የተናገሩትን ሰምቼ በእጅጉ ደነገጥኩ፡፡ ተሳቀቅሁ፡፡ አፈርኩ፡፡ እናም ለራሴ፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ በጣም አዘንኩ፡፡

ወደ አሜሪካ የተጓዘው የቅንጅት ልዑካን ቡድን አምስቱ አመራር አባላት፣ ከቅንጅት ፕሬዚዳንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ጋር የሃሳብ ልዩነት ውስጥ መግባታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በአንዳርጋቸው ፅጌና በብርሃነ መዋ ስውር ደባ የተለያየ መድረክ እየተዘጋጀላቸው በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ቡድን ላይ ፀያፍ ተግባር የሚፈፅመው አምስቱ የቅንጅት ልዑካን አባላት አደግዳጊዎቻቸውን በአጃቢነት አስከትለው ጭራሹን መረን ወጡ፡፡ እናም ካናዳ ውስጥ በተካሄደ አንድ ስብሰባ ላይ እንዲህ እስከማለት ድረስ ዘቀጡ፡፡ “<u>…ደደብ ጭንቅላት መብሰሉ ላይቀር ማገዶ ይፈጃል</u>” (ሠረዝ የእኔ)

ይህንን ፀያፍ አባባል የተናገረው አርቲስት ደበበ እሸቱ ነው፡፡ አርቲስት ደበበ እሸቱ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል እንደሆነ ልብ በሉ፡፡ የቅንጅት ም/ፕሬዚዳንት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የአርቲስት ደበበ እሸቱን ፀያፍ እና ስድ አባባል የተቃረነች መስላ ሌላ መረን ለቀቀች፡፡ “…<u>ግመሎቹ ይሄዳሉ፣ ውሾች ይጮሀሉ</u>” አለች፡፡ “አልሸሹም ዞር አሉ” አለ የሀገሬ ሰው፡፡ ወዲያው የደበበ እሸቱ አባባል ይደገም ተባለና አጨብጫቢዎቹ አጨበጨቡ፡፡ እኔ ይህንን ሁኔታ ስሰማ በእጅጉ ደነገጥኩ፡፡ ከድንጋጤ ስሜት ስወጣ የሚከተለው የቻይናዎች ተረት ታወሰኝ፡፡ ተረቱን ቃል በቃል ባይሆንም በግርድፉ ላወጋችሁ ወደድሁ፡፡ ተገቢ ቦታው እዚህ ጋር ነውና፡፡

ሁለት የቻይና ባህታውያን ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ይጓዛሉ አሉ፡፡ የቻይና ባሕታውያን ጥብቅ ሃይማኖታዊ መመሪያ ያላቸው ናቸው፡፡ ከሰው ጋር በፍፁም አይቀላቀሉም፡፡ ከሴት ልጅ ጋር ለማመንዘር ማሰብ ቀርቶ በዓይን ሙሉ ማየት እንኳ አይቻልም፡፡ በዚያ ላይ የፀሎት ሰዓት ሲደርስ፣ በፍፁም ፀጥታና ተመስጠ ድፍን ሁለት ሰዓት ሙሉ የመፀለይ ግዴታ አለባቸው፡፡

በዚህ ጥብቅ ዲስፕሊን ውስጥ ለዘመናት በእምነት የኖሩት እነዚህ ሁለት ባህታውያን በጫካው መሃል በሚገኝ ወንዝ ዳር ሲደርሱ እጅግ በጣም ውብ የሆነች ሴት ወንዙን መሻገር አቅቷት ስትብረከረክ አዩአት፡፡

ይኼኔ አንዱ ባህታዊ ቀጭን ወገቧን እቅፍ አድርጎ የትንፋሿ ሙቀት አንገቱን እየፈጀው ወንዙን አሻገራት፡፡ በዚያች ቅፅበት ደግሞ የጸሎት ሠዓት ደርሶ፣ ለጸሎት ተቀመጡ፡፡ ድፍን ሁለት ሰዓት ሙሉ ጸልየው፣ ጸልየው ሲያበቁ፣ ቆንጆዋን ሴት ያላሻገራት ጓደኛው እንዲህ አለው፡-

"አንተ እኮ! የሃይማኖታችንን ሕግ ጥሰሃልና ንስሃ ልትገባ ይገባል" ነገሩ የገባው ጓደኛው "እኔ ንስሃ አልገባም፤ ይልቅስ የኃጢአት ኃጢአት የፈፀምከው አንተ ነህና ራስህ ንስሃ ግባ" ሲል መልስ ሰጠው፡፡

"እኔ ቆንጆዋን ሴት አንድ ጊዜ አቅፌ አሻገርኳት፡፡ አንተ ግን ድፍን ሁለት ሠዓት ሙሉ በልብህ ተሸክመሃታል" አለው አሉ በኩራት፡፡

ተረቱ ይኸው ነው፡፡ መልዕክቱ ቁልጭ ቅልብጭ ያለ ነው፡፡ ከተነሳንበት ዋናው ጉዳይ ጋር ስናቆራኘው፣ አንድ ሰው ሌላን ሰው "ደደብ" የማለት ብቃት የሚኖረው እሱ ራሱ ደደብ አለመሆኑን ማስረገጥ ሲችል ነው የሚል ትርጉም ይሠጠናል፡፡

መቼም የቅንጅት የአምስቱ ልዑካን ቡድን አባላትና አደግዳጊው አርቲስት ደበበ እሸቱ በዚህ ፀያፍ ንግግራቸው ራሳቸው "ደደብ" አለመሆናቸውን ሊያስረግጡልን አይችሉም፤ አልቻሉምም፡፡ እንደእኔ፣ እንደእኔ ለአርቲስት ደበበ እሸቱ በሃይማኖታዊውም ሆነ በሰዋዊ ሕሊናዊ ሕግ ሌላውን ሰው "ደደብ" ማለት ኃጢአት መሆኑን መናገር ለቀባሪው ማርዳት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ አባባል ደግሞ በእጅጉ የሚያሳፍር ነው፡፡ ነገሮችን ወይም የሌሎች ሰዎች አባባል ለማስተካከል ቢፈልጉ እንኳ የራሳቸው የሆነ፣ ከሌሎች ተለይተው የሚታወቁበት አባባል በተጠቀሙ ነበር፡፡ "ግመሎቹ ይሄዳሉ፣ ውሾቹም ይጮሀሉ" የሚለውን አባባል የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከአምስት ወይም ከስድስት ዓመት በፊት ሲናገሩ እንደሰማሁ አስታውሳለሁ፡፡ ያኔ በዚህ አባባላቸው ተናደንባቸውና ተቆጥተንባቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አባባል በዓላማም በዒላማም የሚለዩአቸውን ተቃዋሚዎች የሸነቆጡበት ስለነበር አግባብነት ሊኖረው ይችል ይሆናል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን "ውሾች" ማለት የደፈሩት በዓላማም፣ በዒላማም የሚመስሏቸውን የትግል ጓደኞቻቸውን መሆኑ ያሳፍራል፡፡ ከላይ ለማለት እንደሞከርኩት፣ ሌሎችን "ውሻ" ለማለት፣ ቀድሞ ነገር ተናጋሪው ራሱ "ውሻ" አለመሆኑን ማረጋገጥ ነበረበት፡፡ ነገር ግን ሊሆን አልቻለም፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ባለፍንበት የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ፣ የናፈቀንና ወደፊትም የምንናፍቀው የመሪዎቻችን አንደበት የተገራና የማያስቆጣ እንዲሆን ነው፡፡ መሪዎቻችን ከኃይለ ቃል እና ከተሳዳቢነት ወጥተው ጨዋ የተገሩና አግባቢ እንዲሆኑ የምንሻ ነበርን፣ ነንም፡፡ የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በንግግራቸው

ሲያስቆጡን ፊታችንን አዙረንባቸዋል፡፡ የእነ ወ/ሪት ብርቱካን ቅንጅት የተሻለና የተገራ ነው ብለን ባመንንበት ወቅት ከእጅ አይሻል ዶማ እንዲሉ፣ ያው ሆነው ስናገኛቸው እኛ ኢትዮጵያውያን አለመታደላችን ያሳዝነኛል፡፡ ይቆጨኛል፣ ያንገበግበኛል፡፡ እና ማንን አምነን ማንን ደግፈን ለለውጥ እንታገል? ያሳስበኛል፡፡

ከሶስት ዓመት በፊት ቅንጅት ተስፋ ነው፣ ቅንጅት ፍቅር ነው፣ ቅንጅት ሠላም ነው፣ ቅንጅት ሕይወት ነው፣ ቅንጅት ዕድገት ነው፣... ወዘተርፈ ሲባል እውነት ነው ብለን አምነን ነበር፡፡ ማመን ብቻ አይደለም እኔም ይህንኑ ስል ኖሬአለሁ፡፡ ለካ ያመንኩት ወይም ያመንነው የራሳችንን ሕልም ነው፡፡

ለእኔ ቅንጅት ሰላም ነው ሲባል፣ ቅንጅት ፍቅር ነው ሲባል ቅንጅት ተስፋ ነው ሲባል.... በመነጋገር፣ በጨዋነት፣ በመወያየት የሚያምንና ለተሻለ ሕይወት የሚተጋ ጠንካራ እና በሳል አመራር የሚሰጥ ነው ብዬ በፍፁም ልቤ አምኜ ነበር፡፡ ዛሬ በቅንጅት ውስጥ የተሰበሰቡ አመራሮች፣ እኛ ምሁራን የምንላቸው፣ እንኳንስ ለእኛ ፍቅር፣ ተስፋ፣ ሠላም ሊሆኑ ቀርቶ በራሳቸው ውስጥ የተፈጠረውን ልዩነት እንኳ በአግባቡ መፍታት ያልቻሉ ሆነዋል፡፡ **ቅንጅት "መንፈስ" ነው በሚል ንግግሯ በሕዝብ ዘንድ እውቅና ያገኘችው ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ያንን ጠንካራ የቅንጅት መንፈስ ከሕዝቡ ልብ ውስጥ ለማውጣት መራወጧ በእጅጉ ያሳዝናል፡፡**

በመሠረቱ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የስልት፣ የስትራቴጂና የአመለካከት ልዩነት ሊፈጠር ይችላል፣ መፈጠርም አለበት፡፡ ቁም ነገሩ እንዲህ ዓይነቱን ልዩነት በሰከነ፣ በረጋና በመግባባት መንፈስ መፍታት መቻል ነው፡፡ ልዩነትን በመነጋገር፣ በመወያየት፣ በመግባባት መፍታት ያልቻለ ድርጅት በአሸዋ ላይ የተገነባ ቤት ማለት ነው፡፡ በንፋስም በወጀብም ሊፈርስ ይችላልና፡፡ ቅንጅት ዛሬ ዛሬ እንዲህ እየሆነ ነው፡፡ ታዲያ እንዴት ነው ፓርቲው ከላይ የተጠቀሱትን ሰዎች ይዞ ሀገርና ሕዝብን ሊመራ የሚችለው? እንዴት ነው የነገዋን ኢትዮጵያ ሊረከብ ይችላል ብለን ተስፋ የምናደርገው?

እኔ በግሌ ተስፋዬ እየተሟጠጠ ነው፡፡ በተለይም ወይ አሜሪካ በተጓዘው አምስቱ የቅንጅት ልዑካን ቡድን አባላትና በአደግዳጊዎቻቸው አንደበት ለከት ማጣት፣ አለመስከንና የአስተሳሰብ ግልብነት የተነሳ፣ በወደፊቷ ኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ተስፋ እቆርጥ ዘንድ ተገድጃለሁ፡፡ **የትግል ጓደኞቹንና አጋሮቹን "ደደብ" ለማለት የደፈረ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል፣ የዓላማና የዒላማ አጋሮቿን "ውሻ" ለማለት የደፈረች የቅንጅት ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንትና ሌሎችም አደግዳጊዎቻቸው፣ ነገ ከነገ ወዲያ በክብር ከፍ ከፍ ያደረጋቸውን ሕዝብ፣ የእነሱን ዓላማ ተከትሎ የተሰዋውን፣ የቆሰለውን፣ የተሰቃየውን ወገን እናውቅህም አለማለታቸው አለመሳደባቸው፣ አለማንጓጠጣቸው ምን**

ማረጋገጫ አለን? ምንም፡፡ ስለዚህም ነው የዚህ ፅሁፍ ርዕስ “ቅንጅት - ደበበ ደደበ” ለማለት የደፈርኩት፡፡ ይህንን በማለቴ አዝናለሁ፡፡ አበቃሁ!